መግቢያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማው ቻርተር አዋጅ የተሰጡትን ስልጣኖችና ኃላፊነቶች ለመወጣት እንዲሁም ፈጣንና ሁሉን አቀፍ ልማት እውን ለማድረግ በርካታ ህዝባዊ አገልግሎቶችን እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል።

በከተማው ውስጥ የሚገኙ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች የዕለት ተዕለት የኑሮ ጫና ለማቃለል፣ *መሠረታዊ* የፍጆታ ዕቃዎችና የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ እንዲደርሱ ለማድረግ፣ እንዲሁም ስትራቴጂካዊ ፋይዳ ያላቸው የመንግስት ልማት ድርጅቶች አቅም ተጠናክሮ ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል ከማዕከላዊ በጀት የሚደረግ የድጎማ ድጋፍ ወሳኝ ድርሻ አለው፣

ይሁን እንጂ እስካሁን ሲተገበር የቆየው የድጎማ በጀት አጠያየቅ እና አፈቃቀድ ስርዓት በሳይንሳዊ መስፈርቶች ላይ የተመሰረተ እንዲሆን በማድረግ በኩል ክፍተቶች የነበሩበት በመሆኑ፤ የበጀት አጠቃቀሙን ግልጽነትና ተጠያቂነት ማረጋገጥ አስፈልጓል፣

በመሆኑም የከተማ አስተዳደሩ ፋይናንስ ቢሮ የተሻሻለውን የከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995፣ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 16/2009 አንቀጽ 76 እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 94/2019 ክፍል አራት አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 1 /ሀ/ የሰጡትን ስልጣን መሠረት በማድረግ ይህንን ረቂቅ *መመሪያ* አዘጋጅቷል፣

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 1. የመመሪያው ርዕስ

“የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት በጀት ድጎማ ጥያቄ አቀራረብና አፈቃቀድ መመሪያ ቁጥር .../2019”

አንቀጽ 2. ትርጓሜ

1. “ከተማ አስተዳደር” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው።

2. “ቢሮ” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ ነው።

3. “ድጎማ” ማለት በከተማ አስተዳደሩ በጀት አዋጅ መሰረት ህዝባዊ አገልግሎቶችን መሠረታዊ የፍጆታ እቃዎችን እና የልማት ስራዎችን ለህብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ ወይም የተቋማትን የአሰራር አቅም ለማጠናከር ከማዕከላዊ በጀት የሚመደብ የገንዘብ ድጋፍ ወይም ማካካሻ ነው።

4. “ተጠቃሚ ተቋም” ማለት ከከተማ አስተዳደሩ የበጀት ድጎማ እንዲደረግለት በህግ ወይም በውል የተፈቀደለት የከተማ አስተዳደሩ መዋቅራዊ ተቋም፣ የህዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ወይም የመንግስት ልማት ድርጅት ነው።

አንቀጽ 3. የመመሪያው አስፈላጊነትና መነሻ

1.የድጎማ በጀት አጠያየቅ እና አፈቃቀድ ስርዓት በመመሪያ የተደገፈ ለማድረግ

2.ከቢሮው ለድጎማ የሚመደበውና የሚለቀቀው ገንዘብ በተሟላ የወጪና ገቢ ጥናት እና በግልጽ መስፈርቶች ላይ ተመስርቶ እንዲመደብ ለማድረግ

3.የሚመደበው የድጎማ በጀት ለታለመለት ዓላማና ለተጠቃሚው ማህበረሰብ መድረሱን የሚያረጋግጥ የክትትል ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ

4.ስትራቴጂካዊ ፋይዳ ያላቸው የመንግስት ልማት ድርጅቶች የካፒታልና የቴክኖሎጂ እጥረት ሳይገድባቸው ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጡ ለመደገፍ

አንቀጽ 4. የመመሪያው ዓላማ

1. የድጎማ በጀት ጥያቄዎች በሳይንሳዊ ጥናትና በገበያ ዋጋ ክፍተት ትንተና ላይ ተመስርተው እንዲወሰኑ ለማድረግ፣

2. የድጎማ ተጠቃሚ ተቋማት ወጪን የመቀነስ፣ የራሳቸውን ገቢ የማሳደግ እና አሰራርን የማዘመን ግዴታ እንዲወጡ ለማድረግ፣

3. የድጎማ ገንዘብ የሚለቀቅበትን ቅድመ-ሁኔታዎች በማስቀመጥ ገንዘቡ ለታለመለት ዓላማ ብቻ እንዲውል ለማድረግ፣

አንቀጽ 5. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ከከተማ አስተዳደሩ ማዕከላዊ በጀት የፋይናንስ ድጎማ በሚጠይቁ የድጎማ ተጠቃሚ ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል ።

ክፍል ሁለት

የድጎማ ዓይነቶችና ምደባ መስፈርቶች

አንቀጽ 6. የድጎማ ዓይነቶች

በዚህ መመሪያ መሰረት በከተማ አስተዳደሩ በጀት የሚደረጉ ድጎማዎች በሚከተሉት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ፦

ሀ/ መሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎችና አቅርቦቶች ድጎማ

በከተማው ውስጥ እንደ ዳቦ፣ የምግብ ዘይት፣ ዱቄት እና ሌሎች በህዝብ ፍጆታ ላይ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው መሠረታዊ እቃዎች ለህበረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲደርሱ በልዩ ሁኔታ ከአምራቾች ወይም ከአቅራቢዎች ጋር በመተባበር ለሚደረግ የዋጋ ልዩነት ማካካሻ የሚውል ድጎማ፣

ለ/ የህዝብ ትራንስፖርት ድጎማ

የከተማውን ህበረተሰብ ዕለታዊ የትራንስፖርት ጫና ለማቃለል ሲባል የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ሰጪዎችን እና የአሠራር ወጪ ለመደገፍ፣ የነዳጅ ዋጋ መናርን ለማስተካከል እና የትራንስፖርት ታሪፍ ተመጣጣኝ እንዲሆን ከማዕከላዊ በጀት የሚሰጥ የሥራ ማስኬጃና የካፒታል ድጎማ፣

ሐ/ የመንግስት ልማት ድርጅቶች የካፒታል ድጎማ

ስትራቴጂካዊ ጥቅም ላላቸው እና ለከተማው ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ወሳኝ ለሆኑ የመንግስት ልማት ድርጅቶች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለማስገባት፣ የማምረት አቅማቸውን ለማሳደግ እና የካፒታል እጥረት ለማቃለል የሚሰጥ ልዩ የድጎማ ማዕቀፍ።

አንቀጽ 7. የድጎማ አቀራረብና ምዘና መስፈርት

ሀ/ ድጎማ የሚጠይቅ ማንኛውም ተቋም የወጪ እና የገቢ ትንተና፣ የድጎማ ፈላጊው ህበረተሰብ ብዛት እና መጠን፣ የድጎማውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ የሚያሳይ የድጎማ ፍላጎትና የዋጋ ክፍተት ጥናት ለቢሮው ማቅረብ አለበት።

ጥናቱ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፦

i. የእቃው ወይም የአገልግሎቱ ትክክለኛ የአመራረት ወይም የአቅርቦት ወጪ

ii. በገበያ ላይ ያለው ነባር ዋጋ እና ለህበረተሰቡ እንዲቀርብ የታቀደው የተመጣጣኝ የሽያጭ ዋጋ

iii. በሁለቱ ዋጋዎች መካከል ያለው የፋይናንስ ልዩነት እና የሚጠየቀው የበጀት መጠን።

ለ/ የድጎማ ጥያቄ የምዘና መስፈርቶች

i. ጥያቄው የተሻሻለው የከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 እና የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 51/2009 ለቢሮው የሰጡትን ስልጣን ያገናዘበ መሆኑ

ii. ጥያቄው ከከተማ አስተዳደሩ አጠቃላይ የአምስት ዓመት የልማት ዕቅድ፣ ከድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች እና ከከተማው ማህበራዊ አጠቃላይ ግቦች ጋር የተጣጣመ መሆኑ መረጋገጥ አለበት

iii. ከተቋሙ የቀረበው የምርት ፣ አገልግሎት ፣ የአመራረት ወይም አቅርቦት ነጠላ ወጪ በትክክለኛ የሂሳብ አሰራር የተሰላ እና በገበያ ላይ ካለው ዋጋ ታሳቢ ያደረገ ስለመሆኑ

iv. ተቋሙ የራሱን ገቢ ለመሰብሰብ ያደረገው ጥረት እና ያለውን አቅም የመጠቀም ደረጃ በመገምገም ተቋሙ ከራሱ ገቢ በላይ የሆነ የፋይናንስ ክፍተት ስለመኖሩ

v. የወጪ ጫናውን በድጎማ ከመሸፈን ይልቅ አሰራርን በማዘመን፣ ብክነትን በመቀነስ ወይም የታሪፍ ማስተካከያ በማድረግ መሸፈን ስለመቻሉ

vi. ድጎማው በቀጥታ ዝቅተኛ ገቢ ያለውን ህብረተሰብ ክፍል የሚጠቅም መሆኑ መረጋገጥ ስለመቻሉ

ክፍል ሶስት

ኃላፊነትና ተግባራት

አንቀጽ 8. የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊነትና ተግባራት

ሀ/ በየዓመቱ ከሚጸድቀው የከተማ አስተዳደሩ ማዕከላዊ በጀት ውስጥ ለድጎማ የሚሆን አጠቃላይ የበጀት መጠን በማዘጋጀት ለካቢኔ ወይም ለከተማው ምክርቤት ያቀርባል ሲፀድቅ ለተጠቃሚ ተቋማት የድጎማ በጀት ይመድባል

ለ/ ከድጎማ ተጠቃሚ ተቋማት የድጎማው ዓይነት ጋር የተጣጣመ መስፈርት ማዘጋጀት፣

ሐ/ የድጎማ ገንዘብ እንዲመደብ ወይም እንዲሰጥ ሲወሰን ቢሮው ከተጠቃሚ ተቋማት ጋር የዕቃዎች ጥራት፣ የተመጣጣኝ ዋጋ ወሰን፣ እና የጊዜ ሰሌዳን ያካተተ የውጤት ስምምነት ይፈራረማል፣

መ/ ከድጎማ ተጠቃሚ ተቋማት ለቢሮው የሚቀርበው የድጎማ ገንዘብ ጥያቄ ገንዘቡ በትክክል ለታለመለት ዓላማ የሚውል መሆኑን ወይም መዋሉን፣ የህብረተሰቡ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ መሆኑ ተገልፆ ሲቀርብ ብቻ ነው፣

ለ/ የድጎማ ተጠቃሚ ተቋም ኃላፊነትና ተግባራት

i. የወጪ፣ የገቢ፣ የገበያ ዋጋ ክፍተት እና የህብረተሰቡን ፍላጎት መጠን በግልጽ የሚያሳይ ዝርዝር የድጎማ ጥናት ሰነድ ለቢሮው ያቀርባል፣

ii. ከመንግስት የተሰጠውን ድጎማ በመጠቀም ህዝባዊ አገልግሎቶችን ወይም መሠረታዊ እቃዎችን ለታለመለት ህብረተሰብ ክፍል በተቀመጠው የተመጣጣኝ ዋጋ ማድረሱን ያረጋግጣል፣

iii. የድጎማ በጀትን ከሌሎች የመደበኛ የገቢ ምንጮች ጋር ሳይቀላቀል በልዩ የሂሳብ መዝገብ በመያዝ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ አለበት፣

iv. በተሰጠው የድጎማ ገንዘብ የተደረገውን የዕቃ ስርጭት፣ የአገልግሎት ሽፋን እና የፋይናንስ አጠቃቀም አፈፃፀም ሪፖርት በቢሮው ጥያቄ ሲቀርብለት ማቅረብ ይጠበቅበታል፣

ክፍል አራት

የድጎማ አፈፃፀም፣ ክፍያ እና የቁጥጥር ስርዓት

አንቀጽ 9. የድጎማ ክፍያ አፈፃፀም ስርዓት

i. የድጎማ ክፍያ የሚፈጸመው በየዓመቱ በከተማው ምክር ቤት በሚጸድቀው የበጀት አዋጅ እና በዚሁ መሰረት በተመደበው የበጀት ጣሪያ ወሰን ውስጥ ብቻ ይሆናል

ii. የድጎማ ገንዘብ የሚለቀቀው ተቋሙ ከዚህ ቀደም የተለቀቀውን በጀት ለታለመለት ዓላማ ማዋሉን የሚያሳይ አፈፃፀም ሪፖርት ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል

አንቀጽ 10. የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት

ሀ/ የድጎማ ተጠቃሚ ተቋማት የተመደበላቸውን የድጎማ በጀት ከሌሎች የራሳቸው የገቢ መለያዎች ጋር በተገቢ ሁኔታ ለይተው መያዝ እና ለታለመለት ዓላማ ብቻ ማዋል አለባቸው።

ለ/ ከድጎማ ተጠቃሚ ተቋማት የድጎማ ዋጋ ማሻሻያ ጥያቄ ለቢሮው ሲቀርብ ቢሮው የድጎማ ገንዘቡ አጠቃቀም፣ በዕቃዎች ስርጭት ሂደት እና በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የማጣራት ስራ ማካሄድ ይችላል

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 11. ተጠያቂነት

ይህንን መመሪያ ተላልፎ የተገኘ፣ የድጎማ ገንዘብ ያለአግባብ ያዋለ፣ ያባከነ ወይም በህገ-ወጥ መንገድ ያከፋፈለ ወይም የሐሰት አፈፃፀም ሪፖርት ያቀረበ ማንኛውም አካል በከተማ አስተዳደሩ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ በኩል ተጠያቂ ይሆናል።

አንቀጽ 12. መመሪያ ስለማሻሻል

ቢሮው ይህን መመሪያ በሚመለከታቸው ሕጎችና በአስተዳደራዊ ሥርዓቶች መሠረት ሊያሻሽል ይችላል።

አንቀጽ 13. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በከተማ አስተዳደሩ ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ጸድቆ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፤

አብዱልቃድር ሬድዋን

በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ

አዲስ አበባ